የልጅ ደህንነት ቀጣይነት ያለው የህጻናት እንክብካቤ (CWCCC)

ወላጆች እና አሳዳጊዎችን በተመለከተ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች



Child Welfare Continuing Child Care (የልጅ ደህንነት ቀጣይነት ያለው የህፃናት እንክብካቤ, CWCCC) ምንድን ነው?

CWCCC በ Working Connections Child Care (የስራ ግንኙነቶች የልጅ እንክብካቤ) ፕሮግራም በኩል የልጅ እንክብካቤ ድጎማ ፕሮግራም ነው። CWCCC የ12 ወራት የልጅ እንክብካቤ ይሰጣል። ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች የግድ "በተፈቀደ ተግባር" ውስጥ መሆን የለባቸውም እና የግድ ምንም አይነት የገቢ መስፈርቶችን ማሟላት አያስፈልጋቸውም። ለ12 ወራት ወርሐዊ የጋራ ክፍያ (ኮፔይ) የለም።

CWCCC እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

የጉዳይ ክትትል ሠራተኛዎ ሪፈራሉን ለማድረግ ፈቃድዎን ያገኛል። የጉዳይ ክትትል ኃላፊዎ ሪፈራሉን ከላከ በኋላ **በ 1-844-626-8687 ወደ Working Connections በመደወል** ሪፈራሉን መሙላት አለብዎት። የ12 ወራት የልጅ እንክብካቤ ሪፈራልዎን ካጠናቀቁበት ቀን አንስቶ ይጀምራል።

ልጄ የልጅ እንክብካቤ ከመጀመሩ በፊት ለ Working Connections ካልደወልኩ ምን ይከሰታል?

ለልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎ የሚደረጉ ክፍያዎች የሚጀምሩት የልጅ እንክብካቤ ሪፈራሉን ሞልተው ሲያጠናቅቁ ነው። ሪፈራልዎ ከመጠናቀቁ በፊት CWCCC ለልጅ እንክብካቤ መክፈል አይችልም። ሪፈራልዎን ለማጠናቀቅ ወደ Working Connections ካልደወሉና ልጅዎ የልጅ እንክብካቤ የሚከታተል ከሆነ፣ ለሚከታተልበት ጊዜ መክፈል ይኖርብዎታል።

የእኔ ጉዳይ ክትትል ሰራተኛ የCWCCC ሪፈራል ቢያደርግም በወቅቱ የልጅ እንክብካቤ አላስፈለገኝም ነበር ወይም በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ነበርኩ፤ ሆኖም ግን፣ አሁን ለመጀመር ዝግጁ ነኝ። ምን ማድረግ አለብኝ?

የCWCCC ሪፈራልዎን ለማጠናቀቅ ጉዳይዎ ከተዘጋበት ጊዜ ጀምሮ ስድስት ወራት አሉዎት። ከስድስት ወር በላይ ከሆነ፣ ለCWCCC ብቁ አይደሉም፤ ለተለየ ፕሮግራም ግን ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ለማወቅ፣ በ1-844-626-8687 ለWorking Connections ይደውሉ።

ምን ዓይነት የልጅ እንክብካቤ ዓይነቶች ይፈቀዳሉ?

በዋሽንግተን ስቴት ውስጥ ያለ ወይም በአይዳሆ ወይም አሪገን ውስጥ ባሉ የአሳራቢች ከተሞች የድጎማ ክፍያዎችን የሚቀበል ማንኛውም የተፈቀደለት የልጅ እንክብካቤ ማዕከል ወይም ፈቃድ ያለው የቤተሰብ ቤት። Family, Friends, and Neighbor Care (ቤተሰብ፣ ጓደኞች እና የሳረቤት እንክብካቤ, FFN) ለCWCCC ብቁ አይደለም፤ ነገር ግን፣ ይህንን በ1-844-626-8687 Working Connections በመደወል ማግኘት ይችላሉ።

ከ 12 ወራት በኋላ የልጅ እንክብካቤ ካስፈለገኝ ምን ይሆናል?

እንደገና እንዲያመለክቱ የሚጠይቅ ደብዳቤ ከWorking Connections (የስራ ግንኙነቶች) ይደርስዎታል። መረጃ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ እንዲሁም ለሌላ ፕሮግራም ብቁ መሆንዎን ለመወሰን ይገመገማሉ። ስለእነዚህ መሥፈርቶች የበለጠ ለማወቅ፣ ወደ **www.dcyf.wa.gov/services/earlylearning-childcare/getting-help/wccc** ይሂዱ።

ከልጅ የደህንነት ስርዓት ከልጅ ጋር ምግዚትነትን እየተቀበልኩ/እያቋቋምኩ ነው። ብቁ ነኝ ወይ?

የCWCCC ፕሮግራም የተዘጋጀው የDCYF የልጅ ደህንነት ጉዳይ ላላቸው ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ብቻ ነው። ለሌላ የልጅ እንክብካቤ እርዳታ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። እባክዎ ከጉዳይ ሰራተኛዎ ጋር በመሆን ሊኖሩ የሚችሉ ዕድሎችን ያጣሩ።

DCYF ለሁሉም ለፕሮግራሞቹ እና አገልግሎቶቹ ዘር፣ ቀለም፣ ጾታ፣ ሃይማኖት፣ እምነት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የዜግነት ሁኔታ፣ የጾታዊ ዝንባሌ፣ እድሜ፣ የውትድርና ሁኔታ፣ ወይም የምንም አይነት አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ ወይም የአዕምሮ እክልን በማየት አያዳላም እንዲሁም እኩል ተደራሽነትን ያቀርባል።

*የዚህን እትም ነጻ ቅጂዎች በአማራጭ ቅርጸት ወይም ቋንቋ ማግኘት ከፈለጉ፣ እባክዎ የDCYF ህዝባዊ ግንኙነቶችን በ1-800-723-4831 ያግኙ ወይም ኢሜይል ወደ **communications@dcyf.wa.gov** ይላኩ።*

DCYF PUBLICATION CWP_0066 AM (06-2023) Amharic

Washington State Department of CHILDREN, YOUTH & FAMILIES